# ገድለ ቂርቆስ
# መኢየሉጣ

## በግዕዝና አማርኛ

## የጣና ሐይቅና መንፈሳዊ እሴቱ


<u>አዘጋጅ እና አሳታሚ</u>

ርዕሰ ገዳማት መአድባራት ጣና ቅዱስ ቂርቆስ
አንድነት ገዳም (ጣና ሐይቅ) 2011ዓ.ም

# መልክአ ቂርቆስ
# በአማርኛ

ብርሃናዊ ፀሐይ ብርሃኑን እስኪያጨልም ድረስ
መከራን የተቀበልህ ክርስቶስ ሆይ! በመስቀል
የፈሰሰ ደምህን ቀለም አድርገህ የመንፈሳዊ ቂርቆስ
የዜናውን መጽሐፍ የመልክኡንም ሰላምታ በልቤ
ሰሌዳ ጻፍ።

## ለዝክረ ስምከ

ሕጻን ቂርቆስ ሆይ! ትርጉሙ የጣፋጭ ዕፍራን
አበባ ለተባለ የስምህ መታሰቢያ ሰላምታ ይገባል
በሰማያዊ ሥልጣን ነግሦ የሚኖር ይህን ስምህን
በቦታው ሁሉ አንደበቱ በጠራው ጊዜ ሞት ይደንግጥ
ሰይጣንም ይሸሽ።

## ለስእርተ ርእስከ

በራስህ ላይ ለበቀሉና ላደጉ የራስ ጠጉሮችህ
ሰላምታ ይገባል፤ ቂርቆስ ሆይ! የሁሉ ጌታ የክርስቶስ
የበረከቱ ሀብት የቅዱስ መስቀሉም ሞገስ
ለዘላለሙ ካንተ ጋር ይሁን በለኝ።

## ለርእስከ

መላ ፊትህ በደም እስኪታለል ድረስ ከነቆዳው

ለተላጨ ጠጉርህ ሰላምታ ይገባል፤
ሐጻን ቂርቆስ ሆይ! ነፍሴ ከሥጋዬ ተለይታ
በምትወጣ ጊዜ ከሰማይ ወደ እኔ ስትመጣ
የራስህን ዘውድ በራሴ ላይ አኑር።

## ለገጽከ

ከፀሐይና ከጨረቃ ብርሃን ሰባት እጅ ለሚያበራ
ፊትህ ሰላምታ ይገባል፤
ለዘላለም ደስ ብሎህ የምትኖር ሐጻን ቂርቆስ ሆይ!
ኖኅን መርከቡ ከጥፋት ውኃ እንዳዳነችው ጸሎትህ
ከልቅሶና ከዋይታ ታድነኝ።

## ለቀራንብቲከ

ከላይ በታች ላሉ አራቱ ቅንድቦችህ ሰላም እላለሁ፤
ክርስቶስን ሕማሙንና ሞቱን ተናገርህ ሐጻን
ቂርቆስሆይ! ሁሉ ለቤቱ ተግቶ ያስባልና
አቤቱ በአንቱ እንዳትጠፋ ቤተመቅደስህን
ለመጠበቅ ትጋ።

## ለአዕይንቲከ

በመማለል ወደ ላይ ተሰቅለው የብረት ችንካር
ነበልባሉን አይተው ላልደነገጡ ዓይኖችህ ሰላምታ
ይገባል፤ ሐጻን ቂርቆስ ሆይ፤ጽድቁንና የበዛ
ይቅርታውን እንዲሰጠኝ በፍጹም ልብህ የታመንክበት

አምላክን ዘወትር ስለእኔ ለምነው::

## ለአእዛኒክ

ያለፍርሀትና ያለማፈግፈግ የሁለት ችንካሮችን
ሕማም ለተቀበሉ ጆሮዎችህ ሰላምታ ይገባል፤
የድንግል ማርያም ታማኝ የመንፈስ ቅዱስም ወዳጅ
ቂርቆስ ሆይ! አገልጋይህ ከበደል ውድቀት
በትንሣኤ እስክነሣ ድረስ ሦስት ሱባዔ ጸልይልኝ::

## ለመላትሒክ

ከዐላዊ መኮንን እጅ ብዙ ጊዜ መጻፍትን ለተቀበሉ
ጉንጮችህ ሰላምታ ይገባል፤
/ቂርቆስ ሆይ/ ሰይጣንን የሚያሸሽ ሞትንም የሚያስደ
ነግጥ የአብና የወልድ የመንፈስ ቅዱስንም ስሞች
በግምባሬ ላይ ጻፍልኝ ምልክትም አድርግልኝ::

## ለአዕናፊክ

የዐመፃ ማኅበሮች እጆቻቸውን ዘርግተው ሰናፍጭና
ጨው በውስጣቸው ለጨመሩባቸው አፍንጫዎችህ
ሰላምታ ይገባል፤
ሽንጋይ የስጋ ሹምን ያችነፍህ ሕጻን ቂርቆስ ሆይ!
የፈሰሰ ደምህን የተቸነከረ አካልህንም አይቶ
እሱ እግዚአብሔር ገነትን ከፈተልህ::

## ለከናፍሪከ

እንደ መላእክት ምስጋናን ለሚናገሩ ደስ ለተሰኙ
ከንፈሮችህ ሰላም እላለሁ፤
የእስጢፋኖስ ወገን የሰማዕቱ ሚናስም ባልንጀራ
ቂርቆስ ሆይ! ነበልባል ጸሎትህ እሳት
ልመናህም የኃጢአቴን እሾህ ሁልጊዜ ያቃጥልልኝ::

## ለአፉከ

ጥበብና አንደበትን ከፈጣሪ መንፈስ ቅዱስ ለተቀበ
አፍህ ሰላምታ ይገባል፤
አእላፍ ከሀዲዎችን ያቸነፍህ ሶምሶን ቂርቆስ ሆይ!
በጎሊናዬ ማሳ በቅሎ ያደገ ስንፍና በሥልጣንህ
በትእዛዝህም ማጭድ ይቆረጥ::

## ለአስናኒከ

ንጻታቸው እንደበረዶ መልካቸውም እንደመረግድ
(ዕንቁ) ለሆነ ጥርሶችህ ሰላምታ ይገባል፤
የእግዚአብሔር ወልድ ወዳጅ ቂርቆስ ሆይ! በጎሊናዬ
ማሳ በቅሎ ያደገ ስንፍና በሥልጣንህና በትዕዛዝህ
ማጭድ ይቆረጥ::

## ለልሳንከ

በመድኃኒተኛ እጅ ከግንዱ ለተቆረጠ ምላስህ
ሰላምታ ይገባል፤ የጋኑ ነጎድጓድ ያላስፈራህ ቂርቆስ

ሆይ! አብርሃም ይስሐቅ ልጁን እንደባረከው አንድነታ
ችንን /እያንዳንዳችንን/ ዛሬ ባርክ::

## ለቃልክ

ከአፈር ተፈትኖ እንደወጣ የጠራ ብር ከነውር
ለነፃ ቃልህ ሰላምታ ይገባል፤ የጥበበኞች ጥበበኛ
ከዐዋቂዎችም ይልቅ ዐዋቂ የሆንህ ቂርቆስ ሆይ!
ከሰማዕት እስጢፋኖስና ከተወደደ ሚናስ ጋር
በባሕር የታነጸች መቅደስህን ጎብኛት::

## ለእስትንፋስክ

እንደ በረከትና የይቅርታ ነፋስ መዓዛው ለሚያለመል
ም እስትንፋስህ /ትንፋሽህ/ ሰላምታ ይገባል፤
የምስራች ነጋሪ ቅዱስ ወንጌልንም ያስተማርህ
ሕጻን ቂርቆስ ሆይ! በድንግል ማርያም ልጅ መስቀል
እግዚአብሔር ይስማህ በሚል በንጉሥ ዳዊትም ቃል
እኔን ባርከኝ::

## ለጉርዔክ

የሁሉን ልመና ሰምተህ የምትራዳ ቂርቆስ ሆይ!
ለጉረሮህ ሰላምታ ይገባል፤ ከገዳይ ከግፈኛም ሰው
ያድነኝ ዘንድ በምትጠቅም ጸሎትህ የሚያይ እርሱ
ግን የማይታይ እግዚአብሔርን ዘወትር ለምነው::

## ለክሳድከ

በእሳታዊ ሰይፍ አንደበት አጎንብሶ ለተቆረጠ
አንገትህ ሰላምታ ይገባል፤ ሐጻን ቂርቆስ ሆይ!
በዝንጉ እስክንድሮስ ከከሀዲዎች ጭፍራዎቹም ዘንድ
በየጊዜው ያገኘህን መከራና ችግር ስንቱን እናገራለሁ፤

## ለመትከፍትከ

የፈጣሪ የወልደማርያምን ቀንበር መስቀልን
የተሸከመ ትከሻህን ሰላም እላለሁ፤
ቂርቆስ ሆይ! ደስ ያለው የምሥራች ነጋሪ መልአክ
ገብርኤል ከአንተ ጋር ይቅር ባይ በሆነ አምላክ ፊት
ቆሞ ኃጢአቶቼን ያቃልልኝ በደሌንም
ያስተሥርይልኝ::

## ለዘባንከ

ክርስቶስ በሦስት ሰዓት እንደተቀበለ ብዙ
ግርፋትን ለተቀበለ ጀርባህ ሰላምታ ይገባል፤
ቂርቆስ ሆይ የሦስት ዓመት ልጅ ስትሆን ጽኑውን
ድብደባ እንደምን ቻልከው፤
የሚባላው እሳትስ እንደምን አላስፈራህም?

## ለእንግድዓከ

መጽሐፍ እንደሚያመሰግነው እንደ ዕዝራ ልቡና
ለከበደው ደረትህ ሰላምታ ይገባል፤

ሕጻን ቂርቆስ ሆይ! ከእናትህ ጋር በአንድነት
እቶኑን እንደ ጫማ የረገጠው እሳቱንም
እንደውኃ ያቀዘቀዘው እንዳንተ ያለማን ነው?

## ለሕጽንክ

የሊቅ /አለቃ/ ክርስቶስ የሰላሙና የጽድቁ ማኅበሮች
በላይ ለተቀመጡበት ጭንህ ሰላምታ ይገባል፤
ሕጻን ቂርቆስ ሆይ! ቀድሞ የኤፍሬም ልጆች
እንደተገለበጡ በትእዛዝህ ቃል ጠላቶቼ በየጠዋቱ
ይገልበጡ ባላጋራዎቼም ይውደቁ::

## ለአእዳዊክ

በሥቃይና በድካም ሰንሰለት ለቆሰሉና ለደከሙ
እጆችህ ሰላምታ ይገባል፤
የሰማይ ንጉሥ የክርስቶስ ወታደር
ኃያሉ ቂርቆስ ሆይ! ስሚ የጣፈጠ የቡርክት
ማርያም በረከቷንና ሰላሟን እንድቀበል ርዳኝ::

## ለመዛርኢክ

ከአለት ለጸኑ ወርቾችህ የምስክርነት ደምን
ለተረጨ ክርንህም ሰላምታ ይገባል፤
ቂርቆስ ሆይ ይቅር በለው ብለህ የሚራራ
እግዚአብሔርን ስለእኔ ማልደው::

## ለእመትከ ወለእራኁከ

የእግዚአብሔርን ፍቅር ለያዙና ለዳሰሱ ክንድህና
ለመዳፍህ በአንድነት ሰላምታ ይገባል፤
ጥበብና ዕውቀትን የተመላህ አስተዋዩ ሐጻን ቂርቆስ
ሆይ! አቤቱ የአንደበቴን ነገር ፈጥነህ አሳርግ
የአፌንም ምስጋና አሳስብ::

## ለአጻብዒከ

አሥሩ ጣቶችህን ከጥፍሮቻቸው ጋር ሰላም
ሰላም ሰላም እላቸዋለሁ፤
ዋናተኛ ቂርቆስ ሆይ! ጤግሮስ ልቅሶና ግዮን ኀዘን
እነሆ በዚህ ዘመን ኅሊናየን አስጥመውታልና
ፍጹም ፀጥታ ወዳለበት አሻግረኝ::

## ለገቦከ የማናዊ

ለቀኝ ጎንህ ዳግመኛም ለግራ ጎንህ ሰላም እላለሁ፤
በአካል ሕጻን በጥበብ ብዛት ግን አረጋዊ የሆንህ
ቂርቆስ ሆይ! ቀድሞ ዕብራዊው ሙሴ ግብጻዊውን
ሰው እንደገደለው ጠላቴን /ሰይጣንን/ ፈጥነህ አጥፋው

## ለከርሥከ ወለልብከ

የመከራ የሥቃይ እንጀራን ራት ላደረጉ ሆድህና
ልብህ በአንድነት ሰላምታ ይገባል፤
ቂርቆስ ሆይ! የአፌን ቃል የተወደደ አድርግልኝ፤

የለመንሁህንም ብዙውን ነገር ለአምላክ አሳስበው
ዘወትርም ንገረው።

## ለኩልያቲክ ወለጎሊናክ

ከበቀልና ከቂም ለራቁ ኩላሊትህና ጎሊናህ
ሰላምታ ይገባል፤
ተአምረኛው ቂርቆስ ሆይ! ምልክዓም እንደተባለ
እንደሙሴ ፈርዖን ኃጢአቴን በሚያሰጥም
የሥርየት ባሕር ወርውረው አስጥመውም።

## ለአማዑቲክ ወለንዋየ ውስጥክ

በሰማይ ሆድህ መካከል ለተሰቀሉ (ላሉ)
አንጀትህና ሆድዕቃህ ሰላምታ ይገባል፤
ጨለማ ክህደትን የምታስወግዳት ፀሐይ ቂርቆስ ሆይ!
የእናትህን ቀጸላ በራሴ ላይ አዙር፤
የእናትህ የኢየሉጣንም አክሊሏን ስጠኝ።

## ለጎንብርትክ

በአንጀትና በልብ መካከል ያለች አንዲት
እንብርትህን ሰላም እላለሁ፤
ሕጻኑ ቂርቆስ ሆይ! ለሚች በግህ ከዚህች ዘመን
መከራ ከበዛ የአሳች ሰይጣንም ሥራው ጠባቂ ሁነኝ።

## ለሐቄክ

ዝናር ሃይማኖቱን ታጥቆ የገዝ እስክንድሮስ

ወርቹን ለቀጠቀጠ ወገብህ ሰላምታ ይገባል፤
ለቲቶ መምህር ለጳውሎስ ወገን የሆንህ ባለሽቱ
ልሳን ቂርቆስ ሆይ! ለንጉሥ ሠራዊቱን ለእረኛው
መንጋውን ይጠብቅ ዘንድ አምላክን ማልደው ይቅርታ
ውንም ለምን::

## ለአቂያጺክ ወለአብራኪክ

በጥበበኛ አንጥረኛ እጅ ለተሰራ ለአጽሎን ላልተገዙ
ጭኖችህና ጉልበቶችህ ሰላምታ ይገባል::
የመንፈስ ቅዱስ ልጅ የሳውልና የኬፋ ወንድም
ቂርቆስ ሆይ! ማኅበሮችህ ከአንተ ጋር
ስለገድላቸውና ትዕግሥታቸው አልፋ በተባለ
በክርስቶስ ፊት ተስፋን አገኙ

## ለአዕጋሪክ

የቀያፋ ባልንጀራ በሆነ በእስክንድሮስ አደባባይ
መታሠርን ለተቀበሉ እግሮችህ ሰላምታ ይገባል::
የመንፈስ ቅዱስ ልጅ የሳውልና የኬፋ ወንድም
ቂርቆስ ሆይ! ማህበሮችህ ከአንተ ጋር ስለገድላች
ውና ትዕግሥታቸው አልፋ በተባለ በክርስቶስ ፊት
ተስፋን አገኙ::

## ለሰኰናክ ወለመከየድክ

በሥቃይ ጎዳና ለተመላለሱ ተረከዝህና
የውስጥ እግርህ በምስጋና ሰላምታ ይገባል፤

ቂርቆስ ሆይ! አንተ ሀሴተኛ አገልጋይ መኮንን
ኃጢአትና መስፍን በደል ለዘመናት ገዙህ
ይበቃል ብለህ አርነት አውጣኝ።

## ለአጻብዒከ ወለአጽፋሪከ

የሥቃይ ዐጸድን የመከራንም ቦታ ለረገጡ
ጣቶችህና ጥፍሮችህ ፈጥኜ ሰላምታ አቀርባለሁ፤
ብርሃንን የተጎናጸፍህ ሙሽራው ቂርቆስ ሆይ!
በምድርና በሰማይ እኔ ሳለሁህ ልጄ ሆይ
ስለምን ሐዘንን ታበዛለህ በለኝ።

## ለቆምከ

ቅላቱ እንደ ሮማን ቅላት ለሆነ በምድር ለሚያቅላላ
በሰማይም ለሚያበራ ቁመናህ ሰላምታ ይገባል፤
ሕጻን ቂርቆስ ሆይ! እንደወደድከኝ እረዳበት ዘንድ
ልቤ በሚሻው ልክ የሦስቱን አካላት /የሥላሴን/
በረከት በንግግርህ ስጠኝ።

## ለመልክእከ

በዮርዳኖስ ውኃ ለተጠመቀ የሰላምና የእርቅ ቅባት
ሜሮንንም ለተቀባ መልክህ ሰላምታ አቀርባለሁ፤
ቂርቆስ ሆይ! ሠለስቱ ደቂቅ እሳቱን እንዳቀዘቀዙ
በነጎድጓድ፤ ጸሎትህና በመብረቅ ልመናህ
የሚቀጣጠል የእሳቱን እቶን ነበልባል አቀዘቀዝህ።

## ለጸአተ ነፍስ

ከሀዲ መኮንን ሥጋህን በገደለ ጊዜ ሊገድላት
ላልቻለ ለነፍስህ መውጣት ሰላምታ ይገባል፤
ቂርቆስ ሆይ! የለመንሁህን ልመና ሰምተህ
ከሁሉ ይልቅ ሲኦልን እፈራለሁና በወንጌል
እኖር ዘንድ ከጽድቅህ ጽድቅን አድለኝ::

## ለበድነ ሥጋከ

ለአምላክ ሕግ በቀና በኤልያስ ሰረገላ ተሰውሮ ላለ
ሥጋህ ሰላምታ ይገባል::
ለኃጢአተኛ የምትማልድ የአስተማሪዎች አስተማሪ
ቂርቆስ ሆይ! በመስቀል ላይ በተሠዋ/ ራሱን
በሠዋ አምላክ/ ዘንድ መተላለፌን አስተሥርይልኝ
በደሌንም በየሰባቱ ሰባ ጊዜ አስቀርልኝ

## ለሕማምከ

እንደርጎሩጎ ክርስቶስ መገፋት ልብን ለሚያስለቅስ
መከራህና የበዛ መገፋትህ ሰላምታ ይገባል፤
የደስታዬ ክረምት ቂርቆስ ሆይ! የልቅሶና የዋይታ
ሰው በምሆን በእኔ ላይ ለሦስት ወራት ያህል የደስታ
በረከትህና የንጹህ ዝናም ነጠብጣብ ያንጠባጥብ::

## ለነቅዓ ደምከ

የመከራው ዜና በሚያስደነግጥ በመስቀሉ በግ

በክርስቶስ ደም ለተረጨ ለደምህ ምንጭ
ሰላምታ ይገባል፤
የሰማዕታት ወንድም የሐዋርያትም ልጃቸው
ቂርቆስ ሆይ! መታሰቢያህን ለሚያደርጉ
የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ስጣቸው ከአምላክህ
ዘንድ የጽድቅን ዋጋ አዘጋጅላቸው።

## ለህላዌከ

እሳታውያን በሚሆኑ ሰባቱ ነገድ መካከል ለሆነ
አኗኗርህ ሰላምታ ይገባል፤
ቂርቆስ ሆይ! ቤትህ በታነጸበት በአንተም
ዐጸድ የሚገድል ችነፈር ለዘላለሙ እንዳይመጣ
በአብና በወልድ መንበር ፊት አማልድ።

ላማረ ቁመናሽ በመንፈስ ቅዱስ ሰላምታ ሰላምታ
ይገባል፤
መዐዛሽ የጣፈጠ ገነት ኢየሉጣ ሆይ!
ዝናም ከደመና እንደሚፈስስ የጡቶችሽ ወተት
ዛሬ በአፌ ውስጥ ይፍሰስ።

ለአርባ ሦስት መልኮችሽ ለአራቱም ባሕርዮችሽ
ሰላምታ ይገባል፤
የቂርቆስ እናት የከበርሽ ኢየሉጣ ሆይ!
በከንቱ እንዳልጠፋ ምሕረቱ የበዛ የጽድቅ አምላክ
እግዚአብሔርን ስለእኔ ለምኚው።

ይህን የማነሴት ቃል ይህንንም ድርሳን በእጅ
የጻፈውን በአንደበት ያነበበውን ቃላቶቹንም
በእዝነ ሥጋ በእዝነ ልቡና የሰማውን የሕጻን
ቂርቆስ የከበሩ ጣቶቹ በብርሃን ክርስቶስ
ሥልጣን በአንድነት ይባርኩን።

እነሆ ከገድሉ አውጥቼ የቂርቆስንና የወገኑ ኢየሉጣን
መልክዕ ጻፍሁ፤
የሁሉ እመቤት ማርያም ሆይ! ባርኪልኝ፤
በምድር የባረክሽው በሰማይ የተባረከ ነውና
የቀደስሽውም ለዘላለም ይኖራልና።

መባርቅትና ነጎድጓድን የምትይዝ ሆይ!
እሳቱን ስላቀዘቀዘ ስለ ሕጻኑ ኪዳን ከቸነፈር ታደገን፤
ይህችንም ዐጸድ ከወራሪ ቸነፈር ታድናት ዘንድ
በምስክርነት ደሙ ተማጽነናል።

ፊተኛውና ኋለኛው /አልፋና ዖ/ ሆይ!
ቂርቆስን በጠራነው ጊዜ በደለኛውን አውሬ እናቸንፈው
ዘንድ በምስክርነት ደሙ ተማጽነናል ቤትህ
ከተሠራበት ቸነፈር አይምጣ ብለህ ቃል
ገብተህለታልና ከቸነፈር ፍላጻ እንድንድን
አቤቱ ደግፈን።

ሕጻንና እናቱ ሁለቱም ገድላቸውን ፈጸሙ
የጋኑ ድምፅ እንደክረምት ነጎድጓድ ነበር የከበሩ

ሰማዕታት ግን ሞትን አልፈሩትም።

የኢየሉጣ ልጅ ብፁዕ ቂርቆስ ወደ እቶኑ (ጋኑ) ለመግባት አልፈራም፤ ጌታም ቤትህን በጽኑ እምነት ከሚሠራ ሰው ቸነፈርን አስወግዳለሁብሎ የምህረት ኪዳን ሰጠው።

አካለ መጠን ያላደረሰህ ቂርቆስ ሆይ!
ከጓደኛህ ከሚናስ ጋር ሰላም እልሀለሁ፤
የዮናስ ቅል በሌሊት በቅላ ከዋዕየ ፀሐይ ግለት
እንደጋረደችው በደመና ረድኤትህ ዘወትር ጋርደኝ።

የቅዱስ ቂርቆስ የእናቱም የኢየሉጣ አምላክ ሆይ
አገልጋይህ_____ን ከጥፋት ዘመን
ከክፉም ቀን ጠብቀኝ አድነኝም ሠውረኝ ታደገኝም።

የከሀዲዎች ቁጣ ወደ እቶን ለመግባት ያላስፈራህ
መልክህና ደምግባትህ ያማረ ሕጻን ቂርቆስ ሆይ !
ሰላም ላንተ ይሁን።

ተአምርህ የከንፈሮች ቃል የነገርም መብዛት ፈጽመው
ከባሕር አሸዋና ከሣር ይልቅ የበዛ ነው፤
ሰላም ላንተ ይሁን!

ሥራህን እስኪያደንቁ ድረስ በእስክንድሮስ አደባባይ
ጫማውን በራ ያደረግህ ከአንገቱም ፍየልን ያወጣህ
ሆይ ሰላም ላንተ ይሁን።

ስምህ ያማረ ቂርቆስ ሆይ ውኃ ቀለም
ሆኖ ቢጻፍ እንኳ ዓለም ተአምርህን ባልቻለው
ነበር፤ ሰላም ላንተ ይሁን::

ቂርቆስ ሆይ ጥቂት እጅ መንሻ ስላቀረብኩልህ
ፈንታ በደስታ አደባባይ እቆም ዘንድ::
የመጋደልህን ዋጋ አብዝተህ ስጠኝ::

ቂርቆስ ሆይ ሰላም ላንተ ይሁን
በምቆምበት ጊዜ በየሰዓቱ በወልድና
በእናቱ ፊት የዚህ ምልጃዬ መልእክተኛ ነህ በለኝ::
ሰላም ላንተ::

ተከዚን የምትተካከል የሰላማችን ወንዝ
ቂርቆስ ሆይ ከሕዝባችን ልብ ማጣትን
ታስወግድ ዘንድ በየጊዜው ለመባረክና
ለማረጋጋት ና ና::

---------- // ----------

# ገድለ ቂርቆስ መኢየሉጣ

## በግዕዝና አማርኛ

የጣና ሐይቅና መንፈሳዊ እሴቱ


አዘጋጅ እና አሳታሚ

ርዕሰ ገዳማት መአድባራት ጣና ቅዱስ ቂርቆስ
አንድነት ገዳም (ጣና ሐይቅ) 2011ዓ.ም

# ገድለ ቱርቄስ ወኢዮስጣ



ውጸሌ መጣናይ ፣ መጽሐፈ ገድል ፣
መጽሐፈ ተአምር ፣
መልክአ ቲርቆስ ፣ መልክአ ኢየሉጣ
በግዕዝና በአማርኛ

ተርጓሚ - መምህር ኃይሉ ኤርምያስ
ጥር ፲፱፻፺፯ ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የሐዋኑ ሰማዕት የቅዱስ ቂርቆስና
# የእናቱ ቅድስት ኢየሉጣ ገድል
## መልክአ ቂርቆስ በማዕዝ እና በአማርኛ



# ገድለ ቅዱስ ቂርቆስ
# ወእሙ ኢየሉጣ

## በግእዝ እና በአማርኛ



ተርጓሚ፦ መጋቤ ሐዲስ መምህር ተስፋ ሚካኤል ታከለ

፳፻፲፩ ዓ.ም